

# ዮናስ

*.እግዚአብሔር ዮናስን ወደ ታላቂቱ ነነዌ ከተማ በመሄድ የንስሐ ስብከት እንዲሰብክ አዘዘው። ዮናስ ግን ለመሄድ ፈቃደኛ አልነበረም። ከእግዚአብሔር ለመሸሽም በተቃራኒ አቅጣጫ ለመጓዝ ሞከረ።

* መርከብ ላይ ተሳፈረ። እግዚአብሔርም መርከቧ ልትሰጥም ትንሽ እስኪቀራት ድረስ ኃይለኛ ማዕበልን አስነሳ። በመርከቧ ላይ የነበሩ ሰዎች ለዚህ ሁሉ መንስኤው ዮናስ መሆኑን ሲረዱ ዮናስን ከመርከቡ ውስጥ አውጥተው በባህሩ ላይ ጣሉት።

* እግዚአብሔርም ዮናስን የሚውጥ ትልቅ አሳ ነባሪ አዘጋጀ። ዮናስም በአሳ ነባሪው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደእግዚአብሔር ፀለየ። በአሳ ነባሪው ሆድ ውስጥ ለሶስት ቀንና ለሶስት ሌሊት ቆየ። ከዚያም አሳ ነባሪው በደረቅ ምድር ላይ ተፋው።

* እግዚአብሔርም እንደጋና ዮናስ ለነነዌ ሰዎች እንዲሰብካቸው አዘዘው።ዮናስም ታዘዘው። እጅግ ታላቅ ከተማ ነበረች። ዮናስ የከተማይቱን ሰዎች ንስሐ ካልገቡ ከተማይቱን እንደሚያጠፉት ነገራቸው። ሰዎቹም ዮናስ የነገራቸውን አምነው ተቀበሉት። ስለኃጢአታቸው ተፀፁ። እግዚአብሔርም ይቅት አላቸው።

* ዮናስ ግን ደስተኛ አልነበረም። እጅግ በጣምም ተቆጣ። ስለነነዌ ከተማ ሕዝብም ሆነ ስለታላቂቱ ከተማ ነነዌ ምንም ግድ አልነበረውም። እግዚአብሔር ግን በጣም ይወዳቸው ነበር።

* ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 12፡ 30 ላይ ስለዮናስ ተናግሯል። የዮናስን በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ መቆየትና የእርሱን በመቃብር ውስጥ ለሶሰት ቀናት መቆየት አነፃፅሮ ተናግሯል።

የዮናስን ታሪክ በብሉይ ኪዳን በመፅሐፈ ዮናስ ምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 4 ድረስ ማንበብ ትችላላችሁ።

http://gardenofpraise.com